ጥቅምት 17 2002 ዓ.ም

## ረሃብን ለግል መሰሪ ፖለቲካ መጠቀም በሕግ ያስጠይቃል!!

የዴሞክራሲ ሥርዓትን መገንባት ብቻ ሳይሆን ባለፉት ዓመታት በተከታታይ ሁለት አሃዝ ያለው የኤኮኖሚ እድገት አስገኝቻለሁ እያለ የመለስ አገዛዝ መጠነ ሰፊ የሆነ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ ባለበት በአሁኑ ወቅት ይህ የተባለው እድገትና ዴሞክራሲ ከተጻፈበት ወረቀትና ከተነገረበት የዜና ተቋም አልፎ ወደታች ዘልቆ የሕዝቡን የልብ ትርታና ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ የሙብቱ ተጠቃሚና የእድገቱ ተቋዳሽ አድርጎት ኑሮውን ካለበት ከፍ ሊያደርገው ግን አልቻለም። ቀድሞዉንም ቢሆን የመለስ አገዛዝ እየወሰዳቸው ያሉ ድርጊቶች በሕዝቡ ፍላጎትና ይሁንታ ላይ በመንተራስ የተቀየሱ ፖሊሲዎች አልነበሩምና፤ አሁንም አይደሉምና ውጤታቸው ካሁን በፊት እንደተከሰተው ሁላ በአሁኑ ወቅትም ወደ 14 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ለረሃብ አደጋ ተጋልጦ ይገኛል።

ከዓመት ወደ ዓመት በተሸጋገርን ቁጥር በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን በረሃብ አለንጋ እየተገረፉ፤ በኑሮ ውድነት እየተጠቁ ናቸው፡፡ መሰረታዊ የሆኑ የምግብ ፍጆታ ዋጋ ማሻቀብ የተነሳም ከድህነት ወለል በታች ለመኖር የተገደደውና ሕይወቱን ለማትረፍ ሲልም እርዳታ ፈላጊው ቁጥር እየጨመረ መሆኑ በገሃድ የሚታይ ሊደበቅ የማይችል ሁኗል። የድርቅ፡ የረሃብና የሞት ጥላ በሕዝባችን ላይ ማንዣበብ ከጀመረ ወራቶች አልፈዋል። የኤኮኖሚ እድገት ፕሮፓጋንዳውን የሚጻረር የረሃብተኛውን ቁጥር መግለጹ ደግሞ ለወያኔ ከፍተኛ የራስ ምታት ቢሆንበትም የድርቁንና የረሃቡን ችግር በትክክል ስፋቱንና ጥልቀቱን ለመገመትና ለችግሩም ተገቢውን መፍትሄ ማግኘት እንዳልቻለ እየታወቀ የወያኔ አገዛዝን ከጃንሆይና ከደርግ አገዛዝ የተሻለ፤ ለአርሶ አደሩ ቅን አሳቢ አድርጎ ለማቅረብ እየተደረገ ያለው ጥረት ውሃ የማይቋጥር አሳዛኝና አስቂኝም ትርዒት ነው። በድርቅ ሳቢያ የምግብ እህል እጥረት መድረስ፣ በእህል ዋጋ ውድነትና በገንዘብ እጦት የተነሳ እህል ለመሸመት አቅም አንሶት፤ የረሃብ ጠኔ የሚያንገላታው፤ የሚላስ የሚቀመስ ምግብ ብርቁ የሆነው፤ ንጹህ ውሃ መጠጣት፣ ሰውነትን መታጠብም ሆነ ልብስን አፀዳድቶ መልበስ የማይችለው ዜጋ ቁጥሩ በከተማም በገጠርም በርካታ ነው።

ረሃብ በኢትዮጵያ እየደጋገመ ሕዝባችንን እየጎበኘ ያለው፣ ልዩ ልዩ የምግብ ዓይነቶችን እየዘራና እያመረተ ለሸማቹ አቅራቢ የሆነው አርሶ አደር ስንፍና የተጠናወተው በመሆኑ አይደለም። ተፈጥሮ አመጣሽ ችግር እንዳለ ሆኖ (ይህም ቢሆን መልካምና ለአርሶ አደሩ ተቆርቋሪ የሆነ አስተዳደር ቢኖር ለመቋቋም የሚያስቸግር አይሆንም) ዋናው መንስኤ ገበሬው እርሻውን በዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴ ስኬታማ ለማድረግ የሚያስችለው መልካም አስተዳደር፣ እንዲሁም የፖለቲካና የኤኮኖሚ ነጻነት፤ የተሟላ የጤንነት እንክብካቤ አለማግኘቱ መሆኑም ነው። ይህንን ሁሉ የነፈገው የመለስ አገዛዝ፤ ገበሬው የሚያርሰውን መሬት በባለቤትነት በመያዝና ከገበሬው ፍላጎት ጋር የማይስማማ ፖሊሲዎች ተግባራዊ በማድረጉ ለተደጋጋሚ ረሃብ የዳረገው ለመሆኑ ሀገር ወዳዱና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቀናኢ የሆነው ዓለም አቀፍ የሰላም ወዳድ ኃይል ሁሉ በማስረጃ በማስደገፍ የሚስማሙበት እንደሆነ ግልጽ ነበር። አሁንም ነው። የውጭ እርዳታ ከመጠየቅ፤ የሰውን እጅ ከማየት ዛሬም ቢሆን ሕዝብን ለመታደግ ያልተቻለው በዋናነት ተጠያቂው ሌላ ሳይሆን የመለስ አገዛዝ ራሱና ራሱ የገነባው ሥርዓት ብቻ መሆኑን ለመካድ የሚፍጨረጨሩ ያሉ ቢኖሩም ሃቁ ሃቅ ነውና ይህንን ለማስተባበል ግን በኢሕአፓና በሀገር ወዳዱ ኃይል የጠበቀ የማጋለጥ ተግባር የሚቻላቸው አልሆነም።

ባለፉት ጊዜያት ረሃብ መከሰቱን ለመካድ ሲፍጨረጨር የነበረውና ረሃብ አለ የሚሉትን ነጋ ጠባ እየከሰሰ የሚገኘው የመለስ አገዛዝ ለረሃብ አደጋ የተጋለጠውን ዜጋ ቁጥር አስመልክቶ በጣም ዝቅ በማድረግ ወደ 6.2 ሚሊዮን ቢያደርሰውም ለነዚህ ዜጎቻችንም ቢሆን ከፍተኛ ርብርቦሽ ሳይደረግ አደጋውን ተቋቁመው ቢያንስ እንደበፊቱ ኑሯቸውን ሊቀጥሉ የሚችሉበት ሁናቴ ሊያገኙ እንደማይችሉ ያለፉት ተመክሯችን የሚያስገነዝቡን ናቸው። የቁጥር ብዛትን ማስተባበል መፍትሄ የሚያስገኝና የራሱን ድክመት የሚሸፍንለት ይመስል ከእርዳታ ለጋሾች ጋር አጉል ንትርክ የገባው የመለስ አገዛዝ፤ የነሱን እንቅስቃሴ ለመግታት ቀደም ብሎ በደነገገው ጸረ ዴሞክራሲ ሕግ በመመስረት እነሱ እርዳታቸውን ለማቅረብ በማይደርሱበት አካባቢ ችግሩ ይበልጥ እየተባባሰ በመሄዱ የተነሳ በርካታ ዜጎች ሕይወታቸው ማለፉ ታውቋል። ቀድሞዉኑ በምግብ እጥረት የተጎዱ ሕጻናት

ለተለያዩ በሽታዎች ተጋልጠው መሰቃየት የእለት ተእለት ገጽታ ከመሆን አልፎ በሞት አፋፍ ላይ የሚገኙ በርካታዎች ናቸው።

የእርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች በገቡት ቃል መሰረት እርዳታቸውን ባይለግሱንም ያገኘነውን እርዳታ እያብቃቃንና ከራሳችን አቅም ጋር በማቀናጀት ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የተከሰቱት አይነት አደጋዎች እንዳይከሰቱ ለማድረግ ችለናል እያለ ቢለፍፍም ሃቁ ሌላ መሆኑን ሕዝባችን በሚገባ የሚያውቀው ነው። ገጠርን ማዕከል ያደረገ፤ ገጠር ተኮር ፖሊሲ እከተላለሁ ቢልም ይህ ግን ሕዝብን ከረሃብ አደጋ በዘላቂነት ሊታደግ የሚችል ፖሊሲ የሌለው መሆኑ በተደጋጋሚ የተከሰቱት የረሃብ አደጋዎች ይመሰክራሉ። በተለይ በረሃብ ለተጎዳው ሕዝብ የተሰበሰበን እህል አስመልክቶ የተለያዩ ምክንያቶች እየፈጠረና ለተቃዋሚ ድርጅቶች መልካም አመለካከት ያላቸውንና ድጋፍም ይሰጣሉ በሚላቸው ላይ እየፈጸማቸው ያሉ ድርጊቶች ያስከተሉት ጉዳት፤ ለተራቡት የመጣውን ስንዴና ዘይት ሳይቀር መሸጡ ደግሞ እየተጋለጠበት ይገኛል - በተመሳሳይ ሁኔታ ተከስተው በነበሩት ያለፉት ተመክሮዎች የሚያመላክቱትም ከዚህ ውጭ አልነበሩምና። በቅርቡ ይደረጋል ተብሎ ለሚጠበቀው የምርጫ ተውኔትም እርዳታውን በካድሬዎቹ አማካኝነት ድምጽ ማግኛ አያደርገውም ተብሎ የሚጠበቅም እንደማይሆን ግልጽ ነው። ሕዝብ መራቡ ሳያንስ በእንደነዚህ ዓይነት ድርጊቶች ተጨማሪ በደል ማድረስ ከክፋትም አልፎ አስተዳድረዋለሁ የሚሉትን በረሃብ የተጎዳ የሕዝብ ክፍልን ለሞት መዳረግ ነውና አጥብቆ መታገልን የሚጠይቅ መሆኑ ደግሞ ግልጽ ነው። ረሃብተኛን ለመርዳት ተብሎ በረሃብተኛው ሥም የተገኘ እርዳታን ለግል መሰሪ ፖለቲካ መጠቀም በሕግ የሚያስጠይቅ ነውና ማንም ሀገር ወዳድ በዝምታ ሊያልፈው አይገባም። አግባብነትም የለውም። ስለዚህም ተቃዋሚ ነን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በርግጥም የሥርዓቱ ተቃዋሚነታቸውንና የተሻለ ራዕይ ያላቸው መሆናቸውን ከወረቀት አልፎ ለሕዝቡ በተግባር ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። የሕዝቡን ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ የረሃቡን ጉዳይ የሀገርን ለም መሬት ለባዕዳን አሳልፎ ከመስጠት፤ መሬትን ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ ፖለቲካውንና ኤኮኖሚውን ወያኔ ጨምዶ ከመያዙ ጋር አዛምደው ለሀገር ሉዓላዊነትና ለመልካም አስተዳደር ድምጻቸውን ማሰማት የሚጠበቅባቸው ይሆናል። ሕዝብ ወዳዱን ከጸረ-ሕዝቡ ወያኔ የሚለይበት አንዱ ነጥብ ይህ ነው የሚል የጠበቀ እምነታችን ነው።

ኢሕአፓ መቃወም ሲል የሀገርን ጥቅም አስቀድሞ መዋደቅ እንጂ ከጨቋኝ ጋር መሞዳሞድ ማለት እንዳልሆነ አበክሮ ይገልጻል። ይህንን ለሳቱት በጊዜ ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያ በጋራ እንስጥ ይላል። ወያኔ ካሁን በፊት እንዳደረገው ሁሉ አሁንም ረሃቡን ለራሱ ፖለቲካዊ ጥቅምና ትርፍ ሊጠቀምበት መነሳቱ ከግልጽም ግልጽ ነውና ይህንን መሰሪ ፍላጎቱን በጋራ እንድናከሽፍ ኢሕአፓ ሀገራዊ ጥሪ ያቀርባል። የተጠቁ ወገኖቻችንን በመተባበርና በትግል አንድነት እየታደግናቸው፡ ሀገራችንን የረሃብ ምሳሌ መሆኗን በትግላችን እንዲያከትም እናርገው ይላል ኢሕአፓ።

ሕዝብን ለረሃብ የሚያጋልጥ አገዛዝ ጸረ-ሕዝብ ነው!!


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France